የማይፀና ነው እንኳ ቢባል ዋሱ አመልካች አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ በውል አለመጽናት ምክንያት የሆነው ጉድለት ሳያውቀው ያደረገው የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ግዴታ መሆኑን ያላስረዳ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1923/2/ መሠረት የገባው ዋስትና የፀና ነው ብለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የሥር ፍ/ቤቶች በሥር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሣሽ የነበረው ባት ማስታወቂያ አገልግሎት ድርጅት ለመከሰስ የሚያስችለው ህጋዊ ሰውነት የለውም በሚል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሠረት በማድረግ የሰጡት ዳኝነት የተሻረ ስለሆነ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መዝገብ አንቀሳቅሶ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍ/በ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343 መሠረት መልሰናል፡፡
2. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/ቁ. 10894 ሚያዚያ 22 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. ፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 32599 ሰኔ 06 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ ተሽሯል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር ፋይል ቁጥር 25115

ጥቅምት 5 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡-መንበረፀሐይ ታደሰ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች**፡- አቶ ማሞ ጉበና አልቀረቡም ከተባለ በኋላ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ወርቅነህ ተክለማርያም አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ ለሰበር ሊቀርብ የቻለው የሰበር አመልካች (የሥር ከሣሽ) ግንቦት 28 ቀን 1998 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡

የጉዳዩ የሥር አመጣጥ አመልካች ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአሁኑ የሰበር ተጠሪና (የሥር 2ኛ ተከሣሽ) በሥር 1ኛ ተከሣሽ (ጉዳያቸው በሌሉበት የታየው) ላይ ያቀረቡት ክስ ከሥር 1ኛ ተከሣሽ ለነበሩት በጥቅምት 14 ቀን 1988 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል ላንድሮቨር መኪና በብር 14,000 (አሥራ አራት ሺ.ህ) ሸጠው ከዚህ ውስጥ ብር 10,000 (አስር ሺ.ህ) ተቀብለው ቀሪውን ብር 4,000 (አራት ሺ.ህ) በጊዜ ባለመክፈላቸው ብር 5000 (አምስት ሺ.ህ) አድርገው ለመክፈል ተጨማሪ ውል ማድረጋቸውንና ያሁኑ ተጠሪም ባልተነጣጠለ ሃላፊነት ዋስ በመሆናቸው ዋናውን ገንዘብ ከነወለዱ ከወጪና ኪሣራ ጋር እንዲከፍሉ የሚል ሲሆን ፍርድ ቤቱም ክስና ክርክሩን ከመረመረ በኋላ የሥር 1ኛ ተከሣሽ በቀረበው ክስ መሠረት እንዲከፍሉ፣ያሁኑ ተጠሪ ግን ተራ ዋስ በመሆናቸው በርሣቸው ላይ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1939 መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፣ ውሳኔው በፌ/ከ/ፍ/ቤትም በይግባኝ ፀንቷል፡፡

የሰበር ማመልከቻው የቀረበው የተጠሪን ዋስትና አስመልክቶ በተሰጠው ውሣኔ ላይ ሲሆን ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት ማመልከቻውን ከመረመረ በኋላ በተጠሪ ላይ ያልተወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ሲባል ተጠሪን አስቀርቦ ለማከራከር ያዘዘ ቢሆንም ተጠሪ ለመቅረብ ፈቃደኛ ሆነው ባለመገኘታቸው ጉዳዩን በሌሉበት እንዲታይ አዟል፡፡

በዚህም መሠረት ፍርድ ቤቱ የሰበር ማመልከቻውን ከሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርም[ል፡፡

ከፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ለመረዳት እንደተቻለው ተጠሪ ተራ ዋስ መሆናቸውንና በውሉም ስምምነት ላይ የሥር 1ኛ ተከሣሽ ገንዘቡን ሳይከፍሉ ቢቀሩ ተጠሪ ሃላፊ ሆነው ገንዘቡን እንደሚከፍሉ መገለፁን አስፍሮ በተጠሪ ላይ የቀረበውን ክስ ግን በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1939 መሠረት ውድቅ በማድረግ ተጠሪን በነፃ አሰናብቷል፡፡ ይህ ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1939 እንደተመለከተው የድንጋጌው ንኡስ ቁጥር /1/ ተራ ዋስ በገባው ዋስትና መሠረት ለመክፈል የሚገደደው ዋናው ባለዕዳ ግዴታውን ለመወጣት የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ እንደሆነ ለመረዳት ችሏል፡፡ በሌላም አነጋገር ዋናው ባለዕዳ ግዴታውን ለመወጣት በቂ አቅም (ችሎታ) ያለው እስከሆነ ድረስ ገንዘብ ጠያቂው ዋናውን ባለዕዳ ትቶ ዋሱ ገንዘቡን እንዲከፍለው ለመጠየቅ አይችልም፡፡ ምክንያቱም የተራ ዋስትና ዋናው መሠረት በቅድሚያ ዋናው ባለዕዳ ከገባው ውል አኳያ ግዴታውን እንዲወጣ በመቀጠልም ዋናው ባለዕዳ ግዴታውን ለመወጣት ካልቻለ (አቅም ከሌለው) ተራው ዋስ ገንዘቡን እንዲከፍል ለመስቻል ታስቦ በሕጉ እንዲካተት የተደረገ በመሆኑ ነው፡፡ በተያዘውም ጉዳይ አመልካች ከሥር ጀምሮ ያቀረበው ክስ መስተናገድ የነበረበት ከዚህ ድንጋጌ መንፈስ አኳያ በዚህ ቅደም ተከተል መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ ለእዳው አከፋፈል ዋናው ባለዕዳ ላይ ሃላፊነትን በማስቀመጥና ዋናው ባለዕዳ ለመክፈል አቅም የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ ተራው ዋስ (ተጠሪ) እዳውን እንዲሸከም በሚያስችል መልኩ መወሰን ሲኖርበት ተጠሪ እስከናካቴው ክሱ ካስከተለው ኪሣራና ወጪ ጋር በነፃ እንዲሰናበት መደረጉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡



እንዲያውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1931 ላይ እንደተመለከተው ዋስ የሆነ ሰው በዋናው ባለዕዳ ላይ ክስ ለማቅረብ ገንዘብ ጠያቂው ለመወሰኑ ማስጠንቀቂያ ሲደርሰው ክሱ ለሚያስከትላቸው ወጪዎችም ጭምር ሃላፊ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም በፍ/ብሕ/ቁ.1939 እዳው መከፈል ባለበት ጊዜ ውስጥ ዋሱ ገንዘብ ለባለዕዳው መክፈል እንደሚችል ተገልፆአል፡፡ በመሆኑም በተጠቀሱት ድንጋጌዎች ዋሱ ባንድ በኩል እዳውን በመክፈል ራሱን ነፃ እንዲያደርግና በሌላም በኩል ገንዘብ ጠያቂው ክስ መሥርቶ ከዋናው ገንዘብ በላይ ክሱ ለሚያስከትላቸው ወጪዎች እንዳይዳረግ ከወዲሁ የጥንቃቄ እርምጃዎችን እንዲወሰድ ለማድረግ እንዲያስችሉት መደንገጋቸው ሲታይ ተጠሪ ተራ ዋስ በመሆኑ ብቻ ስለእዳው አከፍፈል ከላይ እንደተመለከተው የቅደም ተከተል ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ከገባው የዋስትና ግዴታ ሙሉ በሙሉ ከሃላፊነት ነፃ የሚሆንበት አንዳችም የሕግ መሠረት እንደሌለ ፍርድ ቤቱ ተገንዝቧል፡፡

በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1939 ተራ ዋስን (ተጠሪን) ሃላፊ አያደርግም በማለት ድንጋጌውን በተሳሳተ አኳኋን በመተርጐም የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.43622 ግንቦት 19 ቀን 1997 ዓ.ም ፣እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት 41054 መጋቢት 1 ቀን 1998 ዓ.ም ተጠሪን በተመለከተ የሰጡት ውሣኔ ተሽ[ል፡፡
2. ተጠሪ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከነወለዱ ኪሣራና ወጪ ጋር የሥር 1ኛ ተከሣሽ ለመክፈል ካልቻሉ ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፣መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ